# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት

Ethiopian Metrology Institute

# የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት

## 2016 በጀት ዓመት የተከለሰ ዕቅድ

ጥር 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ይዘት

1. መግቢያ ........ 1
1.1 የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ገጽታ ........ 1
1.1.1 አመሰራረት ........ 1
1.2 የተቋሙ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች፣ ሥልጣንና ተግባር ........ 2
1.2.1 ተልዕኮ ........ 2
1.2.2 ራዕይ ........ 2
1.2.3 ዕሴቶች ........ 2
1.2.4 በዕቅድ ዘመኑ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዋና ዓላማዎች፣ ........ 2
1.2.5 የኢንስቲትዩቱ ግቦች ........ 3
2. የልማት ዕቅዱ አንድምታዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች ........ 3
2.1 የዓበይት ተግባራት ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት ........ 3
4. የዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት የሚተገበሩ ማስፈጸሚያዎች ........ 20
4.1 የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች ........ 20
4.2 ተቋማዊ የትራንስፎርሜሽን እና የኢኮቴ ዲጂታላይዜሽን አጀንዳዎች ........ 20
4.3 የክትትልና ግምገማ ስርዓት ........ 21
4.3.1 ሪፖርት ........ 21
4.3.2 የአካል ግምገማ ........ 21
4.3.3 ሱፐርቪዥን ........ 21
5. ዕቅዱን ለማሳካት በየምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች ........ 22
5.1 የዝግጅት ምዕራፍ (ሐምሌ-ነሀሴ) ........ 22
5.2 የተግባር ምዕራፍ (መስከረም-ግንቦት 20) ........ 22
5.3 የማጠቃለያ ምዕራፍ (ግንቦት 21 -ሰኔ 30 ........ 22
6. 2016 በጀት ዓመት የፊዚካል እና የፋይናንስ ዕቅድ በየውጤቱ (የጸደቀ በጀት) ........ 24

## 1. መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያን በ2022 ዓ.ም የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ለማድረግ ሀገራዊ ራዕይ ተሰንቋል። በዚህ ረገድ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተቀርፀዉ በየዘርፉ ለተግባራዊነታቸው ከፍተኛ ርብርብ እና ጥረት እየተደረገ ይገኛል። ይህንን የልማት ጉዞ በስኬት ለማጠናቀቅ የሚያስችሉና ለዕድገት አመቺ የሆኑ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ የተደረገ ሲሆን ዕቅዱን ከማሳካት አኳያ ከፍተኛ ኃላፊነት ከተጣለባቸው የኢኮኖሚያዊ ልማት ዘርፎች መካከል በዋናነት የኢንዱስትሪ ልማትና ንግድ ዘርፍ አንዱ ነው።

ምርቶችና አገልግሎቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ በጥራትና በምርታማነት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል በተዘረጋው የጥራት መሰረተ ልማት መዋቅር ውስጥ የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት በዘርፉ ምርምር በማካሄድ፣ ለኢንዱስትሪዎችንና ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የካሊብሬሽን፣ የስልጠናና ምክር አገልግሎት በመስጠት፣ ፍላጎቶቻቸውንና ችግሮቻቸውን በመረዳት አዳዲስ የአለካክ መስኮች በመክፈት እና የሌሎች አገሮች የተሻለ አሰራሮችን ልምዶችን በመቅሰም አስፈላጊውን ሚና ይጫወታል።

በሌላ በኩል የከፍተኛ ትምህርት፣ የምርምር፣ የፍተሻ፣ የጤናና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ምርምር በማካሄድ፣ የመጠቀም አቅም የመገንባት፣ ዘመናዊ የሆነ የሳይንስ መሳሪያዎች የማስተዳደር ስርዓት የመዘርጋት እና የቴክኒክ አገልግሎቶችን (ስልጠና፣ ምክር፣ መረጃ፣ ጥገናና ተዛማጅ ተግባራቶች) የመስጠት ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ ይገኛል።

### 1.1 የኢትየጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ገጽታ

#### 1.1.1 አመሰራረት

በ2001 ዓ.ም በመንግስት በጸደቀው የጥራት መሰረተ-መዋቅር ስትራቴጂ መሰረት የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት እንዲቋቋም በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የካቲት 3 ቀን 2003 ዓ.ም በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 194/2003 ብሄራዊ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩቱ ተቋቁሟል።

በዚህም መሰረት በተለያዩ ተቋማት ይሰሩ የነበሩ ስራዎች ማለትም ከቀድሞው የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለስልጣን የሥነ-ልክ ስራዎችን ፤ ከኢትዮጵያ የጨረራ መከላከያ ባለስልጣን የጨረራ ልኬቶች ትስስር የመጠበቅ ስራ እና የጨረራ ልኬትና ካሊብሬሽን አገልግሎት ስራ እንዲሁም በኢትዮጵያ የሳይንስ መሳሪያዎች ማዕከል ይሰሩ የነበሩትን ተግባራት ሙሉ በሙሉ (የሳይንስ መሳሪያዎች ጥገና፣ ስልጠና፣ የምክርና መረጃ አገልግሎቶች) ከተጠቀሱት ተግባራት ጋር ተስተ ጋብረው በኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ዓላማ ፣ስልጣንና ተግባር ተካተዋል።

### 1.2 የተቋሙ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች፣ ሥልጣንና ተግባር

#### 1.2.1 ተልዕኮ

በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች የጎለበተ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ ችግር ፈቺ ምርምሮችን በማከናወን፣ ቀጣይነት ያለው አቅም በመገንባትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማምጣት ለደንበኞቻችን ብቃት ያለው አገልግሎት በመስጠት የምርትና የአገልግሎት ጥራትና ውጤታማነትን እና በሳይንስ መሣሪያዎች ዘርፍ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው በአፍሪካ ተመራጭ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት መሆን

#### 1.2.2 ራዕይ

በ2022 ዓ.ም በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሣሪያዎች ዘርፍ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው በአፍሪካ ተመራጭ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት መሆን

#### 1.2.3 ዕሴቶች

- ሳይንሳዊ አሰራርን ማስረጽ፤
- ሙያዊ ብቃትና ስነምግባር፤
- ቀጣይነት ያለው መሻሻል፤
- በጎ ህሊናና ቅን ልቦና፤
- ምላሽ ሰጪነት፤
- የዓላማ ፅናት፤
- ሚዛናዊነት፤
- ስትራቴጂካዊ አጋርነት ናቸው፡፡

#### 1.2.4 በዕቅድ ዘመኑ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዋና ዓላማዎች፣

- ችግር ፈቺ ጥናት እና ምርምሮችን ማድረግ
- ከዓለም ዓቀፍ ሥነ-ልክ ስርዓት ጋር የተጣጣመ ብሔራዊ የሥነ-ልክ ስርዓትን የመዘርጋትና በዘርፉ የቴክኖሎጂ ሽግግርን የማምጣት፤
- የአገሪቱን ብሔራዊ የመለኪያ ኢታሎኖችና የተመሰከረላቸውን የማመሳከሪያ ስረቶች ከዓለም ዓቀፍ የመለኪያ ኢታሎኖች ጋር ለማመሳከር፤ለመጠበቅና ለማሰራጨት፤ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋትና የመተግበር፤
- በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳርያዎች ዘርፍ ጥናት እና ምርምሮችን የማከናወንና የመደገፍ፤
- የሳይንስ መሳሪዎችን ጥገና ብሔራዊ አቅም መገንባትና የጥገና አገልግሎት መስጠት፤
- ለሳይንስ መሳሪያዎች ተጠቃሚዎች የቴክኒክ፣ የስልጠናና የምክር የመረጃ አገልግሎቶችን በመስጠት ተግባሮቻቸውን በብቃት እንዲያከናውኑ መደገፍ፤

### 1.2.5 የኢንስቲትዩቱ ግቦች

ግብ 1. የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ
ግብ 2. ተደራሽነትን ማሳደግ
ግብ 3 የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ
ግብ 4 የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት
ግብ 5 አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ
ግብ 6 የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ
ግብ 7 አሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል
ግብ 8 ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል
ግብ 9 የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ
ግብ 10. የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል
ግብ 11 የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል

## 2. የልማት ዕቅዱ አንድምታዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች

የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ሲዘጋጅ የኢንስቲትዩቱን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ እና የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) በጀት ዓመት የልማት ዕቅድ መሰረት በማድረግ ፣ የ2015 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም እና የኢንስቲትዩቱን ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚ እና ስጋትን በመተንተን የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ የመጀመሪያውን ስድስት ወራት በመገምገም እንደሚከተለው ተከልሶ ቀርቧል፡፡ የ2016 በጀት ዓመት የተከለሰው ዕቅድ 11 ስትራቴጂያዊ ግቦችን ያካተተ ሲሆን በግቦቹም ስር ዋና ዋና እና ዝርዝር ተግባራትን አካቶ ይዟል፡፡

### 2.1 የዓበይት ተግባራት ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት

**የተገልጋይ እይታ 40%**
**ግብ 1. የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ**
**1.1 ጥናትና ምርምር ማካሄድ**
**1.1.1** 6 ጥናትና ምርምር ማካሄድ

**1.2 የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት**
**1.2.1** 31000 የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት

**1.3 የጥገና አገልግሎቶች መስጠት**
**1.3.1** ለ300 የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት መስጠት

**1.4 የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት**
**1.4.1** በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለደንበኞች 8 ጊዜ ስልጠና መስጠት

**1.5 የምክር አገልግሎቶች መስጠት**

**1.5.1** በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ 100% የምክር አገልግሎቶች መስጠት

**1.6 የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት**

1.6.1. ለህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ ለሚጠይቁ ደንበኞች ሙሉ በሙሉ አገልግሎት 100% መስጠት

**1.7 የተጠቃሚ እርካታ ጥናት ማድረግ**

**1.7.1** የተገልጋይ እርካታ መመዘን

**ግብ 2. ተደራሽነትን ማሳደግ**

**2.1 በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች የአገልግሎት ወሰን ማስፋትና ማስቀጠል**

2.1.1 በጅማ ቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች በሙቀት አለካክ መስክ የአገልግሎት ወሰን ለማስፋት የላብራቶሪ መሳሪያ ግዢ ማጠናቀቅ

**2.2 የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎቶች መስጠት**

2.2.1 የጥገና ወርክሾፕ እና የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለማቋቋም ጥያቄ ለሚያቀርቡ የግል ባለሃብት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት

**2.3 የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት ለጎብኚዎች ሳቢና ኢንተራክቲቭ እንዲሆን ማድረግ**

2.3.1 ኢንስቲትዩቱን በሚመለከት 12 ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎችን፣ ማዘጋጀት፣ መጫንና ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

2.3.2 የMet/Team ሲስተምን ተግባራዊ በማድረግ የካሊብሬሽን ደንበኞችን የመረጃ አያያዝ አውቶሜት በማድረግ ከደንበኞች አገልግሎት እስከ ፈጻሚዎች ያለውን የመረጃ ልውውጥ ማዘመንና ደንበኞች ባሉበት ሁነው ስራቸው የት እንደደረሰ ክትትል የሚያደረጉበት ሲስተም ተግባራዊ ማድረግ፡፡

**2.4 የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን መስጠት**

2.4.1 በተመረጡ 3 አካባቢዎች (አርባ ምንጭ፣ ፣ ጅማ፣ እና አዋሳ) የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት

**የፋይናንስ እይታ 10%**

**ግብ 3 የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ**

**3.1 የፕሮግራም በጀት ዕቅድ ማዘጋጀት እና የበጀት አጠቃቀም መከታተል**

3.1.1 የፀደቀውን በጀት በዕቅዱ መሰረት 100% መጠቀም

**3.2 የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ**

3.2.1 13 ሚሊዮን ብር የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች ገቢዎችን በማስገባት በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ

**3.3 የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል**

3.3.1 አምስት (5) የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት ማዘጋጀት

**ግብ 4 የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት**

**4.1 ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ መጠየቅ**

4.1.1. የድጋፍ ፕሮጀክት ሰነድ (ፕሮፖዛል) ማዘጋጀት ፣ማጸደቅ እና ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶችን ማፈላለግ

**የውስጥ አሰራር 25%**

**ግብ 5 አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ**

**5.1 ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማስራጨት**

5.1.1 በ5 (በግዝፈት፣ በሙቀት፣ በዳይሜንሽናል፣ በጊዜና ድግግሞሽ እና በግፊት አለካክ መስኮች ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የማነፃፀሪያ መለኪያ መሣሪያዎችን ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅ፣) የአለካክ መስኮች የመጀመሪያ ደረጃ የአለካክ መስኮች ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅ

5.1.2 በዋናው መስሪያ ቤት እና በደንበኞች የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ ለ232 ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማሰራጨት

**5.2 ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች/ወሰን ማስቀጠል**

5.2.1 በላቦራቶሮች ህንጻ ለውጥ ምክንያት ዓለም አቀፍ ዕውቅናቸው በፈቃደኝነት የታገዱት የውስጥ ላቦራቶር (የግዝፈት፣ የኤሌክትሪካል፣ የሙቀት፣ የግፊትና የይዘት) የአለካክ መስኮች እንደገና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት ማደራጀትና ዝግጁ ማድረግ፣

5.2.2 ዓለም አቀፍ ዕዉቅና በነበራቸዉ የውስጥ ካሊብሬሽን(የግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ ግፊትና በይዘት (5))፣ በተንቀሳቃሽ (4) እና በመስክ (2) የካሊብሬሽን የአለካክ መስኮች ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት ማከናወን፣

5.2.3. በሀዋሳ ቅርንጫፍ ላቦራቶሪዎች ዕውቅና ባልተገኘበት በሚዛን ካሊብሬሽን አገልግሎቶች በውስጥ ባለሙያ ኢንተርናሽናል አክሪዲቴሽን ማግኘት

## 5.3 በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት

5.3.1 በወበቅ (Humidity)፣ በእርጥበት (Mositure) እና በኃይል (Force) የአለካክ መስኮች የካሊብሬሽን የአሰራር ስርዓት ሰነድ ማዘጋጀት እና ዕውቅና ማስፋት

5.3.2 በዳይሜንሽናል አለካክ መስክ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት ስልጠናዎች ማግኘትና የካሊብሬሽን የአሰራር መመሪያዎች /Procedures/ መከለስ፣

## 5.4 በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት BIPM-KCDB) ማስመዝገብ

5.4.1 የሙቀት እና የይዘት የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ እንዲመዘገብ ክትትል ማድረግ፣

5.4.2 ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያላቸው የአለካክ መሰኮች የካሊብሬሽን ልኬት ብቃታቸውን /CMC/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ ለማስመዝገብ በሂደት ላይ ያሉ እና አዳዲስ የላቦራቶሮች ቁልፍና ድጋፍ ንጽጽር ፕሮግራሞች መከታተልና መሳተፍ፣

5.4.3 በተገመገመው የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ መሰረት ብቁ የርስበርስ ንጽጽር ውጤት ያላቸው የአለካክ መስኮች /ኤሌክትሪካል/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ ለማስመዝገብ ማመልከቻ ማቅረብ፣

## 5.5 ከአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት ጋር ተሳትፎ ማድረግ

5.5.1 በአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ የቴክኒካል ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ማመቻቸት

## 5.6 የጥራት ስራ አመራር ስርዓቶችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ

5.6.1 ( ISO 9001:2015) ተግባራዊ ለማድረግ ለስራ አመራር አባላት እና ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ስልጠና መስጠት

## ግብ 6 የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ

6.1 የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ

6.1.1 በግዝፈት የአለካክ መስክ የልኬት ትክክለኝነት አሁን ካለበት ከ E2 ወደ E1/E0 ደረጃ ለማሳደግ ስልጠናዎችን በመውሰድ ቅደመ ዝግጅት ማጠናቀቅ፣

6.1.2 በኬሚካል ሥነ-ልክ፣ በፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ እንዲሁም በጊዜና ድግግሞሽ የአለካክ መስኮች በስፔክትሮፎቶ ሜትር አለካክ መስክ የካሊብሬሽን አገልግሎት ለማስጀመር የሚያስችል ስልጠናዎችን በማግኘት ላቦራቶሮችን ማደራጀት፣

## ግብ 7 አሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል

### 7.1 የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ

7.1.1 የሳይንስ መሳሪያዎች የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎትን አውቶሜት በማድረግ ተጠቃሚዎች ባሉበት ሆነው ማመልከት እንዲችሉ እንዲሁም ክትትል ማድረግ የሚያስችል አገልግሎትን ማስጀመር

7.1.2 በተቋሙ ተግባራዊ የተደረጉ የደንበኞች አገልግሎት ሲስተሞችን ተፈጻሚነት ለማዝለቅ ድጋፍና ክትትል ማድረግ

### 7.2 የህግ ክትትልና ድጋፍ አግልግሎት መስጠት

7.2.1 በኢንስቲትዩቱ የሚቀርቡ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን ማቅረብ፣ መከራከር መከታተልና የኢንስቲትዩቱን ጥቅም በህግ አግባብ ማስጠበቅ

7.2.2 ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ቅርጽና ይዘት ማስጠበቅና አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ

7.2.3 የኢንስቲትዩቱን የክፍያ ሰነድ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ

### 7.3 የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዢ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም

7.3.1 በግዥ ዕቅዱ መሠረት ግዥ መፈፀም

### 7.4 የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ

**7.4.1** በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በየዓይነታቸው መለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ማድረግ

**ግብ 8 ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል**

**8.1 ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር በትብብር መስራት**

8.1.1 ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎችና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ለሚመጡ 65 ተማሪዎች ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ማካሄድ

**8.2 ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት**

8.2.1 ከጀርመን (PTB)፣ከደቡብ ኮርያ (KRISS)፣ከደቡብ አፍሪካ (NMISA)፣ ከቱርክ (UME)፣ ከሶማሌላንድ(SQCC) የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር አብሮ መስራት የሚያስችሉ የአሰራር ዘዴዎች በማጥናት ተግባራዊ ማድረግ

**8.3 ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት**

8.3.1 ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት

**መማማርና እድገት 25%**

**ግብ 9 የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ**

**9.1** የሰው ሀብት ልማት ማልማት

9.1.1 ለ200 ኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ስልጠና መስጠት

9.1.2 ለ2 ሰራተኞች ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል መስጠት

9.2 **የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን መከታተልና ማጠናከር**

9.2.1 ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሕፃናት ብር 21600 ድጋፍ ማድረግ

9.2.2 የስርዓተ ጾታ ጋድላይን አፈጻጸም ተግባራዊነት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

**9.3 የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ**

9.3.1 በተቋም ለሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሆኑ አሰራሮች ላይ የተደረገውን ጥናት ተግባራዊ ማድረግ

9.3.2 የተቋሙ የሥነ-ልክ ባለሙያዎች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ማድረግ

## ግብ 10. የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል

### 10.1 የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ

10.1.1 የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአከባቢው የሚያመነጨውን መጠን በየጊዜው በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ

### 10.2 ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት

10.2.1 የጠቅላላ አገልግሎት ስራ ተግባራዊ ማድረግ

### 10.3 የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ

10.3.1 በተቋሙ ተግባራዊ የተደረጉ ልዩ ልዩ ሲስተሞችን (ኢፍሚስ፤ ኢጂፒ፤ ኢስሚስ፤ ኢሜል፤ ዌብሳይት) ደህንነት መጠበቅና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት

10.3.2 የኢንስቲትዩቱን የኔትወርክ መሠረተ ልማት 24/7 ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ እና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት

### 10.4 የለውጥና መልካም አስተዳደር የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት

10.4.1 ተቋማዊ ለውጥ ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ዶክመንት ማቅረብ

10.4.2 የውስጥና የውጭ ቅሬታና አስተያየት በመቀበል እንዲፈቱ ለሚመለከተው ማቅረብና እርምጃ ማስወሰድ

10.4.3 የውስጥ ተገልጋይ እርካታ መመዘን

## ግብ 11 የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል

### 11.1 ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

11.1.1 ግንባታቸው ባለቀ ወይም በከፊል አልቀው ስራ እንዲጀምርባቸው የተወሰኑ ላብራቶሮችን ወርኪግ ቤንቾች እና ሌሎች አስፈላጊ ፋሲሊቲዎች የማሟላት ስራዎችን መከታተልና መደገፍ

### 11.2 የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈጻጸም መገምገም

11.2.1 የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በየደረጃው መፈራረም ፣ በየወሩ አፈጻጸም መገምገም እና ምዘና ማካሄድ

## 3. የ2016 በጀት ዓመት ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር የተከለሰ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2015 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2016 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመታት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 1 | **የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ** | | | | | | | |
| 1.1 | **ጥናትና ምርምር ማካሄድ** | | | | | | | |
| 1.1.1 | 6 ጥናትና ምርምር ማካሄድ | በቁጥር | 4 | 2 | | | | 6 |
| 1.2 | **የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት** | | | | | | | |
| 1.2.1 | 31000 የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት | በቁጥር | 27390 | 31000 | 5601 | 5601 | 9897 | 9901 |
| 1.3 | **የጥገና አገልግሎቶች መስጠት** | | | | | | | |
| 1.3.1 | ለ300 የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት መስጠት | በቁጥር | 252 | 300 | 57 | 58 | 102 | 83 |
| 1.4 | **የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት** | | | | | | | |
| 1.4.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለደንበኞች ስልጠና መስጠት | በቁጥር | 8 | 8 | 2 | 2 | 2 | 2 |
| 1.5 | **የምክር አገልግሎቶች መስጠት** | | | | | | | |
| 1.5.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የሚቀርቡ የአገልግሎት ጥያቄዎች 100% የምክር አገልግሎቶች መስጠት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.6 | **የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት** | | | | | | | |
| 1.6.1 | ለህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ ለሚጠይቁ ደንበኞች ሙሉ በሙሉ አገልግሎት መስጠት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.7 | **የተጠቃሚ እርካታ ጥናት ማድረግ** | | | | | | | |
| 1.7.1 | የተገልጋይ እርካታ መመዘን | በቁጥር | 1 | 1 | | | | 1 |
| 2 | **ተደራሽነትን ማሳደግ** | | | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2015 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2016 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመታት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 2.1 | **በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች የአገልግሎት ወሰን ማስፋትና ማስቀጠል** | | | | | | | |
| 2.1.1 | በጅማ ቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች በሙቀት አለካክ መስክ የአገልግሎት ወሰን ለማስፋት የላብራቶሪ መሳሪያ ግዢ ማጠናቀቅ | በቁጥር | 0 | 1 | | | | 1 |
| 2.2 | **የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት** | | | | | | | |
| 2.2.1 | የጥገና ወርክሾፕ እና የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለማቋቋም ጥያቄ ለሚያቀርቡ የግል ባለሃብት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 2.3 | **የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት ለጎብኚዎች ሳቢና ኢንተራክቲቭ እንዲሆን ማድረግ** | | | | | | | |
| 2.3.1 | ኢንስቲትዩቱን በሚመለከት 12 ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎችን፣ ማዘጋጀት፣ መጫንና ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣ | በቁጥር | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 2.3.2 | የMet/Team ሲስተምን ተግባራዊ በማድረግ የካሊብሬሽን ደንበኞችን የመረጃ አያያዝ አውቶሜት በማድረግ ከደንበኞች አገልግሎት እስከ ፈጻሚዎች ያለውን የመረጃ ልውውጥ ማዘመንና ደንበኞች ባሉበት ሁነው ስራቸው የት እንደደረሰ ክትትል የሚያደረግጉበት ሲሰተም ተግባራዊ ማድረግ፡ | በቁጥር | 0 | 3 | 1 | 1 | | 1 |
| 2.4 | **የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት** | | | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2015 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2016 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመታት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 2.4.1 | በተመረጡ 3 አካባቢዎች (አርባ ምንጭ፣ ፣ ጅማ፣ እና አዋሳ) የግንዛቤማስጨበጫ መስጠት | በቁጥር | 3 | 3 | 1 | 1 | 1 | |
| 3 | **የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 3.1 | **የፕሮግራም በጀት ዕቅድ ማዘጋጀት እና የበጀት አጠቃቀም መከታተል** | | | | | | | |
| 3.1.1 | የፀደቀውን በጀት በዕቅዱ መሰረት 100% መጠቀም | በመቶኛ | 95.5 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 3.2 | **የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ( ክብደት = 1.5)** | | | | | | | |
| 3.2.1 | 13 ሚሊዮን ብር የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች ገቢዎችን በማስገባት በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ | በቁጥር | 11699973 | 13 ሚ | 1950000 | 3050000 | 3600000 | 4400000 |
| 3.3 | **የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል** | | | | | | | |
| 3.3.1 | አምስት(5) የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት ማዘጋጀት | በቁጥር | 5 | 5 | 2 | 1 | 1 | 1 |
| 4 | **የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት** | | | | | | | |
| 4.1 | **ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ መጠየቅ** | | | | | | | |
| 4.1.1 | የድጋፍ ፕሮጀክት ሰነድ (ፕሮፖዛል) ማዘጋጀት ፣ማጸደቅ እና ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶችን ማፈላለግ | በቁጥር | 0 | 1 | | | | 1 |
| 5 | **አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ** | | | | | | | |
| 5.1 | **ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና** | | | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2015 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2016 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመታት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | **ማሰራጨት** | | | | | | | |
| 5.1.1 | በግዝፈት፣ በሙቀት፣ በዳይሜንሽናል፣ በጊዜና ድግግሞሽ እና በግፊት አለካክ መስኮች ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የማነፃፀሪያ መለኪያ መሣሪያዎችን ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅ፣ | በቁጥር | 3 | 5 | 2 | 3 | | |
| 5.1.2 | በዋናው መስሪያ ቤት እና በደንበኞች የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ ለ232 ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማሰራጨት፣ | በቁጥር | 211 | 232 | 42 | 43 | 75 | 75 |
| 5.2 | **ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች/ወሰን ማስቀጠል** | | | | | | | |
| 5.2.1 | በላቦራቶሮች ህንጻ ለውጥ ምክንያት ዓለም አቀፍ ዕውቅናቸው በፈቃደኝነት የታገዱት የውስጥ ላቦራቶር (የግዝፈት፣ የኤሌክትሪካል፣ የሙቀት፣ የግፊትና የይዘት) የአለካክ መስኮች እንደገና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት ማደራጀትና ዝግጁ ማድረግ፣ | በቁጥር | 5 | 5 | | | | 5 |
| 5.2.2 | ዓለም አቀፍ ዕዉቅና በነበራቸዉ የውስጥ ካሊብሬሽን(የግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ ግፊትና በይዘት (5))፣ በተንቀሳቃሽ (4) እና በመስክ (2) የካሊብሬሽን የአለካክ መስኮች ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት ማከናወን፣ | በቁጥር | 11 | 11 | | | | 11 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2015 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2016 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመታት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 5.2.3 | በሀዋሳ ቅርንጫፍ ላቦራቶሪዎች ዕውቅና ባልተገኘበት በሚዛን ካሊብሬሽን አገልግሎቶች በውስጥ ባለሙያ ኢንተርናሽናል አክሪዲቴሽን ማግኘት | በቁጥር | 0 | 2 | | | 2 | |
| **5.3** | **በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት** | | | | | | | |
| 5.3.1 | በወበቅ (Humidity)፣ በእርጥበት (Mositure) እና በኃይል (Force) የአለካክ መስኮች የካሊብሬሽን የአሰራር ስርዓት ሰነድ ማዘጋጀት እና ዕውቅና ማስፋት | በቁጥር | 0 | 3 | | | | **3** |
| 5.3.2 | በዳይሜንሽናል አለካክ መስክ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት ስልጠናዎች ማግኘትና የካሊብሬሽን የአሰራር መመሪያዎች /Procedures/ መከለስ፣ | በቁጥር | 0 | 1 | | | **1** | |
| **5.4** | **በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት BIPM-KCDB)ማስመዝገብ** | | | | | | | |
| **5.4.1** | የሙቀት እና የይዘት የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ እንዲመዘገብ ክትትል ማድረግ፣ | በቁጥር | 0 | 5 | | | | 5 |
| **5.4.2** | ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያላቸው የአለካክ መሰኮች የካሊብሬሽን ልኬት ብቃታቸውን /CMC/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ ለማስመዝገብ በሂደት ላይ ያሉ እና አዳዲስ የላቦራቶሮች ቁልፍና ድጋፍ ንጽጽር ፕሮግራሞች መከታተልና መሳተፍ፣ | በቁጥር | 0 | 5 | | | | **5** |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2015 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2016 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመታት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 5.4.3 | በተገመገመው የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ መሰረት ብቁ የርስበርስ ንጽጽር ውጤት ያላቸው የአለካክ መስኮች /ኤሌክትሪካል/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ ለማስመዝገብ ማመልከቻ ማቅረብ፣ | በቁጥር | 0 | 5 | | | | 5 |
| 5.5 | **ከአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት ጋር ተሳትፎ ማድረግ ( ክብደት = 1 )** | | | | | | | |
| 5.5.1 | በአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ የቴክኒካል ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ማመቻቸት | በቁጥር | 1 | 2 | | | | 2 |
| 5.6 | **የጥራት ስራ አመራር ስርዓቶችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ** | | | | | | | |
| 5.6.1 | ( ISO 9001:2015) ተግባራዊ ለማድረግ ለስራ አመራር አባላት እና ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ስልጠና መስጠት | በቁጥር | 0 | 1 | | | 1 | |
| 6 | **የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 6.1 | **የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ** | | | | | | | |
| 6.1.1 | በግዝፈት የአለካክ መስክ የልኬት ትክክለኝነት አሁን ካለበት ከ E2 ወደ E1/E0 ደረጃ ለማሳደግ ስልጠናዎችን በመውሰድ ቅደመ ዝግጅት ማጠናቀቅ፣ | በቁጥር | 1 | 1 | | | | 1 |
| 6.1.2 | በኬሚካል ሥነ-ልክ፣ በፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ እንዲሁም በጊዜና ድግግሞሽ የአለካክ መስኮች በስፔክትሮፎቶ ሜትር አለካክ መስክ የካሊብሬሽን አገልግሎት ለማስጀመር | በቁጥር | 0 | 3 | | | 3 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2015 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2016 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመታት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | የሚያስችል ስልጠናዎችን በማግኘት ላቦራቶሮችን ማደራጀት፣ | | | | | | | |
| 7 | **የአሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል** | | | | | | | |
| 7.1 | **የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ** | | | | | | | |
| 7.1.1 | የሳይንስ መሳሪያዎች የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎትን አውቶሜት በማድረግ ተጠቃሚዎች ባሉበት ሆነው ማመልከት እንዲችሉ እንዲሁም ክትትል ማድረግ የሚያስችል አገልግሎትን ማስጀመር | በቁጥር | 0 | 3 | 1 | | 1 | 1 |
| 7.1.2 | በተቋሙ ተግባራዊ የተደረጉ የደንበኞች አገልግሎት ሲስተሞችን ተፈጻሚነት ለማዝለቅ ድጋፍና ክትትል ማድረግ | | 0 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 7.2 | **የህግ ክትትልና ድጋፍ አግልግሎት መስጠት** | | | | | | | |
| 7.2.1 | በኢንስቲትዩቱ የሚቀርቡ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን ማቅረብ፣ መከራከር መከታተልና የኢንስቲትዩቱን ጥቅም በህግ አግባብ ማስጠበቅ | በቁጥር | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 7.2.2 | ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ቅርጽና ይዘት ማስጠበቅና አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ | በቁጥር | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 7.2.3 | የኢንስቲትዩቱን የክፍያ ሰነድ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ | | 0 | 1 | | | 1 | |
| 7.3 | **የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዢ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም** | | | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2015 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2016 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመታት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 7.3.1 | በግዥ ዕቅዱ መሠረት ግዥ መፈፀም | በመቶኛ | 1 | 2 | | 1 | | 1 |
| 7.4 | **የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ** | | | | | | | |
| 7.4.1 | በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በየዓይነታቸው መለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ማድረግ | በቁጥር | 1 | 1 | | | | 1 |
| 8 | **ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል** | | | | | | | |
| 8.1 | **ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** | | | | | | | |
| 8.1.1 | ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎችና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ለሚመጡ ተማሪዎች ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ማካሄድ | በቁጥር | 5 | 65 | | | | 65 |
| 8.2 | **ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** | | | | | | | |
| 8.2.1 | ከጀርመን (PTB)፣ከደቡብ ኮርያ (KRISS)፣ከደቡብ አፍሪካ (NMISA)፣ ከቱርክ (UME)፣ ከሶማሌላንድ(SQCC) የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር አብሮ መስራት የሚያስችሉ የአሰራር ዘዴዎች በማጥናት ተግባራዊ ማድረግ | በቁጥር | 3 | 5 | | 2 | | 3 |
| 8.3 | **ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** | | | | | | | |
| 8.3.1 | ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት | በቁጥር | 2 | 2 | | 1 | | 1 |
| 9 | **የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ** | | | | | | | |
| 9.1 | **የሰው ሀብት ልማት ማልማት** | | | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2015 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2016 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመታት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 9.1.1 | ለሠራተኞች ስልጠና መስጠት | በቁጥር | 261 | 200 | 75 | 75 | 50 | |
| 9.1.2 | ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል መስጠት | በቁጥር | 3 | 2 | 1 | | 1 | |
| 9.2 | **የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን ፣ መከታተልና ማጠናከር** | | | | | | | |
| 9.2.1 | ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሁለት የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሁለት ሕፃናት ድጋፍ ማድረግ | በቁጥር | 20694 | 21600 | 5400 | 5400 | 5400 | 5400 |
| 9.2.2 | የስርዓተ ጾታ ጋድላይን አፈጻጸም ተግባራዊነት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 9.3 | **የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ** | | | | | | | |
| 9.3.1 | በተቋም ለሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሆኑ አሰራሮች ላይ የተደረገውን ጥናት ተግባራዊ ማድረግ | በመቶኛ | 1 | 1 | | | | 1 |
| 9.3.2 | የተቋሙ የሥነ-ልክ ባለሙያዎች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ማድረግ | በመቶኛ | 80 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 10 | **የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል** | | | | | | | |
| 10.1 | **የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ** | | | | | | | |
| 10.1.1 | የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአከባቢው የሚያመነጨውን መጠን በየጊዜው በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ | በቁጥር | 1 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 10.2 | **ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት** | | | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2015 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2016 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመታት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 10.2.1 | የጠቅላላ አገልግሎት ስራ ተግባራዊ ማድረግ (ግቢ ውበት፣ፋሲሊቲ እና እድሳት) | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 10.3 | **የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ** | | | | | | | |
| 10.3.1 | በተቋሙ ተግባራዊ የተደረጉ ልዩ ልዩ ሲስተሞችን (ኢፍሚስ፤ ኢጂፒ፤ ኢስሚስ፤ ኢሜል፤ ዌብሳይት) ደህንነት መጠበቅና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 10.3.2 | የኢንስቲትዩቱን የኔትወርክ መሠረተ ልማት 24/7 ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ እና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት | | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 10.4 | **የለውጥና መልካም አስተዳደር የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት** | | | | | | | |
| 10.4.1 | ተቋማዊ ለውጥ ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ዶክመንት ማቅረብ | በቁጥር | 0 | 1 | | 1 | | |
| 10.4.2 | የውስጥ፣ የውጭ ቅሬታና አስተያየት በመቀበል እንዲፈቱ ለሚመለከተው ማቅረብና እርምጃ ማስወሰድ | በቁጥር | 0 | 100 | **100** | 100 | **100** | 100 |
| 10.4.3 | የውስጥ ተገልጋይ እርካታ መመዘን | በቁጥር | 1 | 1 | | 1 | | |
| 11 | **የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል** | | | | | | | |
| 11.1 | **ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ** | | | | | | | |
| 11.1.1 | ግንባታቸው ባለቀ ወይም በከፊል አልቀው ስራ እንዲጀምርባቸው የተወሰኑ ላብራቶሮችን ወርኪግ ቤንቾች እና ሌሎች አስፈላጊ ፋሲሊቲዎች የማሟላት ስራዎችን መከታተልና መደገፍ | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2015 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2016 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመታት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 11.2 | **የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈጻጸም መገምገም** | | | | | | | |
| 11.2.1 | የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በየደረጃው መፈራረም ፣ በየወሩ አፈጻጸም መገምገም እና ምዘና ማካሄድ | በቁጥር | 1 | 2 | 1 | | 1 | |

## 4. የዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት የሚተገበሩ ማስፈጸሚያዎች

### 4.1 የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

- የተዘጋጀውን አደረጃጀት ማጸደቅ እና ምደባ ማከናወን
- ዕውቀት ክህሎትና ሥነምግባር የተላበሰ የሰው ኃይል መገንባት፣
- የውጤት ተኮር ምዘና ስርዓትን በቀጣይነት ተግባራዊ ማድረግ፤
- ከኢንዱስትሪዎች፤ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፤ ምርምርና ስልጠና ተቋማት፤እና ህግ አስፈጻሚ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፤
- ከብሔራዊ፤ አህጉራዊና አለም አቀፍ ተቋማት ጋር ያሉ ትብብሮችን መጠቀም፤
- ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር የአሰራር ሥርዓትን በማሻሻል፣
- በሥነ-ልክ እና የሳይንስ መሳሪያዎች ተግባራት ዙሪያ ለህብረተሰቡ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት፤
- ከተለያዩ ተቋማት የሚደረጉ የመግባቢያ ስምምነቶችን ወደ ፕሮጀክት መለወጥና ተጠቃሚነትን በማስፋት
- የብልሹ አሰራርና አመለካከትን በመቀየር መልካም አስተዳደርና ሥነ-ምግባርን ማስፈን
- በሴክተር ዘለል ተግባራትና የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮችን አካትቶ በመስራት፤

### 4.2 ተቋማዊ የትራንስፎርሜሽን እና የኢኮቴ ዲጂታላይዜሽን አጀንዳዎች

ኢንስቲትዩቱ በደንብ የተሰጠውን ኃላፊነት እና ተግባር በአግባቡ ለመወጣትና በቀጣይ የታቀዱትን ተግባራት ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት ተጠንቶ ለማጸደቅ በክትትል ሂደት ላይ ነው። በተጨማሪም የኢንስቲትዩቱ ማቋቋሚያ ደንብ ጸድቆ ስራ ላይ ከዋለ አስራ አንድ ዓመታትን ያስቆጠረና በአፈጻጸም፣ በአደረጃጀት፣ በተጠሪነት እና በመሰረታዊ ስልጣንና ተግባር ረገድ ውስንነቶች ያሉበት በመሆኑና ይህንንም በመቅረፍ በዘርፉ የሃገሪቱ ፍላጎት አሁን ከተደረሰበት ደረጃ ጋር ማጣጣም በማስፈለጉ እና ለሃገራዊ ልማት የሚያበረክተውን ሚና በብቃት ለመወጣት የካሊብሬሽንና የዕርከን ተዋረድ ትስስር እንዲሁም የጥገና አገልግሎቶች በተጨማሪ በሥነ-ልክና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች የተደረሰበትን የሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ደረጃ በመከተል በዘርፉ የጥናትና ምርምር ተግባራት፣ የማማከር እና የስልጠና ስራዎችን ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ ዓላማው ይህንን እንዲያካትት ተደርጎ ነባሩ ደንብ የተሻሻለ በመሆኑ ለማጸደቅ በክትትል ላይ ነው። የኢኮቴ እና ዲጂታላይዜሽን በተመለከተ የካሊብሬሽን፣የብቃት ማረጋገጫ እና የጥገና አልግሎት (አውቶሜት) E- service አላይን አገልግሎት በ2016 በጀት ዓመት ተግባራዊ ይደረጋል። በተቋሙ የሚገኙ መሠረተ ልማቶችን (ሀርድዌር እና ሶፍት ዌር) አቅም በመጨመር የኢኮቴ ስራውን ለማሳለጥ እየተሰራ ሲሆን በኢንስቲትዩቱ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉትን ሲስተሞችን (IFMIS, ICMIS፣e-GP) አጠናክሮ ለማስቀጠል የክትትል እና ድጋፍ ሥራው በዚህ በጀት ዓመት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

## 4.3 የክትትልና ግምገማ ስርዓት

ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ወይም የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች በአግባቡና በተደረጀ መልኩ መወጣት የሚችለው አስተማማኝ የሆነ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ሲኖረው ነው፡፡ ከዚሁ አንጻር ማንኛውም ተግባር ውጤታማ እንዲሆን ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በዕቅድ ላይ የሰፈሩት ግቦች በተያዘላቸው የሥራ መርሀ-ግብር መሰረት ተገቢውን ግብዓቶች ማግኘታቸውን፣ በመመሪያዎችና ደንቦች መሰራታቸውንና ከታለመለት ዓላማ አንፃር ውጤት ማስገኘቱን ለመመልከትና ለመፈተሽ የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ ይሆናል፡፡

የክትትል ሥርዓት የማያቋርጥ በተከታታይነት የሚከናወን ተግባር ሲሆን በዋናነት የሥራ አፈፃፀሙ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ ለዚሁ ተግባር የዋለውን ሀብት አጠቃቀም፣ የተፈለገው ውጤት ላይ ለመድረስ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ መረጃ ለመስጠት ያገለግላል፡፡ በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ እየሰራባቸው ያሉ የክትትል ሥርዓቶችን በማዳበርና አዳዲሶችን በመዘርጋት በ2016 በጀት ዓመት የተከለሰውን ዕቅድ አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ አቅዷል፡፡ በዚህም መሰረት የክትትልና ግምገማ ስርዓቱ ሶስት መስተጋብሮች ያሉት ሲሆን እነርሱም፡-

### 4.3.1 ሪፖርት

እያንዳንዱ ፈጻሚ ፣ቡድን መሪ እና የስራ ሂደት መሪ ሳምንታዊ እና ወርሃዊ የዕቅድ አፈጻጸም ያቀርባል፡፡ ከሪፖርቱ በመነሳት በየደረጃው ግብረመልስ ይሰጣል፡፡ የተቋሙ ወርሃዊ፣የሩብ ዓመት ፣ የግማሽ ዓመት ፣ የዘጠኝ ወራት እና ዓመታዊ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቶና በስራ አመራር ተገምግሞ ለሚመለከተው አካል ይላካል፡፡

### 4.3.2 የአካል ግምገማ

በየስራሂደቱ ፈጻሚዎች በየሳምንቱ በአካል እየተገናኙ በሚቀርቡ ሳምንታዊ ዕቅድና ሪፖርት መሰረት ስራቸውን ይገመግማሉ፡፡ በተቋም ደረጃ በየሁለት ሳምንቱ ሁሉም የማኔጅመንት አባላት በተሳተፉበት የተቋሙ አፈጻጸም ይገመገማል፡፡ የተቋሙ መሪ ለሁሉም የማኔጅመንት አባላት በአፈጻጸም መከታተያ መሰረት ግብረመልስ ይሰጣል፡፡ በጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት በዘርፍ ደረጃ በየሩብ ዓመቱ ሁሉም የተቋሙ መሪዎች ባሉበት የየተቋማቱ አፈጻጸም ይገመገማል፡፡ ሚኒስትሩም ለሁሉም የተቋሙ መሪዎች ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡

### 4.3.3 ሱፐርቪዥን

የተቋሙ የሱፐር ቪዥን ኮሚቴ በየወሩ አንድ ጊዜ በየስራ ሂደቱ በአካል በመገኘትና ስራውን በመገምገም ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 5. ዕቅዱን ለማሳካት በየምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች

### 5.1 የዝግጅት ምዕራፍ (ሐምሌ-ነሀሴ)

- ዕቅዱን ከፈጻሚ ጋር የጋራ ማድረግ፤
- ዕቅዱን ለየስራ ሂደቱና በእያንዳንዱ ፈፃሚ ድርሻ መዘርዘር፤
- በየደረጃው የመፈራረም ስርአት ማካሄድ፤
- ተግባሩን ለመፈጸም መሰናክል የሚሆኑ ግብአቶችን በመለየት ግዥ ማከናወን፤
- ተገቢውን የክህሎት ስልጠና መስጠት

### 5.2 የተግባር ምዕራፍ (መስከረም-ግንቦት 20)

- በጸረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ትግል እና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ተግባራትን መፈጸም፤
- ጠንካራና የደከሙ አፈፃፀሞች በመለየት፤ የደከሙትን ለማጠናከር የሚያስችል ድጋፍ ይደረጋል፤
- የሪፖርትና የግምገማ ስርዓቶች በትክክል በማከናወን ጥቅም ላይ ማዋል፤5

### 5.3 የማጠቃለያ ምዕራፍ (ግንቦት 21 -ሰኔ 30)

- በዕቅዱ የተያዙ ግቦች መሳካት አለመሳካታቸውን በቢኤስሲ አግባብ መመዘን፤
- ስኬትና ውድቀትን ከማምጣት አኳይ በዝግጅትና በተግባር ምዕራፍ አፈፃፀም ላይ የነበሩ ድክመቶችና ጥንካሬዎች መለየት፤
- ከአሉታዊም ሆነ ከአወንታዊ የተግባራት አፈፃፀም ሊወሰዱ የሚችሉ ትምህርቶች በጠራ ሁኔታ ተለይተው ለቀጣዩ ግብዓት ሆነው እንዲያገለግሉ ይደረጋል፤
- እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ከተሰጠው ተልዕኮ አኳያ ያደረገውን እንቅስቃሴ በጥልቀትና በተጨባጭ አካሄድ ይመዘናል፤
- በአስፈፃሚ አካላት መካከል ግምገማ ይካሄዳል፣ ሂደቱም የመገነባቢያ መድረክ እንዲሆን ከኪራይ ሰብሳቢነት በፀዳ ሁኔታ ይከናወናል፤

6. 2016 በጀት ዓመት የፊዚካል እና የፋይናንስ ዕቅድ በየውጤቱ (የጸደቀ በጀት)

| የፕሮግራም ስም/<br><br>የፕሮግራም ውጤት መግለጫ | የውጤት መለኪያ | 2016 በጀት ዓመት የፊዚካል እቅድ | | | | 2016 ዓመት የፋይናንስ ዕቅድ /በሚሊዮን ብር / | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| **ፕሮግራም 1፡ የሥራ አመራርና ድጋፍ አገልግሎት** | | | | | | | | | |
| ውጤቶች | | | | | | | | | |
| ውጤት 1፡ የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች | በ% | 20 | 30 | 30 | 20 | 6.57 | 10.82 | 5.68 | 4.70 |
| **ፕሮግራም 2፡ የኢትዮጵያ የሥነ-ልክ ስርዓት ዝርጋታና ድጋፍ** | | | | | | | | | |
| ውጤቶች | | | | | | | | | |
| ውጤት 1፡ ያደጉ የአለካክ ወሰኖች | በቁጥር | - | - | 3 | 1 | 1.38 | 2.36 | 1.41 | 1.07 |
| ውጤት 2፡ ዓለም አቀፍ ዕርከን ተዋረድ የጠበቁ ብሔራዊ ማነጻጸሪያዎች | በቁጥር | 2 | 3 | - | - | 0.58 | 0.82 | 1.06 | 0.43 |
| **ፕሮግራም 3፡ ካሊብሬሽንና የልኬት** | | | | | | | | | |
| ውጤቶች | | | | | | | | | |

| የፕሮግራም ስም/<br><br>የፕሮግራም ውጤት መግለጫ | የውጤት መለኪያ | 2016 በጀት ዓመት የፊዚካል እቅድ | | | | 2016 ዓመት የፋይናንስ ዕቅድ /በሚሊዮን ብር / | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| ውጤት 1፡ የተሰጡ የካሊብሬሽን አገልግሎቶች | በቁጥር | 7749 | 7749 | 7749 | 7753 | 3.42 | 4.87 | 2.59 | 0.63 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ፕሮግራም 4፡ የሳይንስ መሳሪያዎች አቅም ግንባታ** | | | | | | | | | |
| ውጤቶች | | | | | | | | | |
| ውጤት 1፡ በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የተሰጡ የስልጠና የማማከር አገልግሎቶች | በቁጥር | 2 | 2 | 2 | 2 | 1.18 | 2.45 | 0.48 | 0.31 |
| ውጤት 2፡ የተሰጡ የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት | በቁጥር | 5 | 5 | 5 | 5 | 0.05 | 0.07 | 0.05 | 0.05 |
| ውጤት 3፡ የተሰጡ የሳይንስ መሳሪያ የጥገና አገልግሎቶች | በቁጥር | 50 | 90 | 90 | 70 | 0.88 | 1.43 | 0.79 | 0.76 |
| ውጤት 4፡ የተሰጡ የምህንድስና አገልግሎቶች | በቁጥር | 5 | 15 | 15 | 5 | 0.12 | 0.98 | 0.57 | 0.02 |